# *የክርስቲያን ሃይማኖት መግለጫ*

## ፩፡ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ።

እኔ ሁሉን በሚችል ሰማይና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ። ደግሞም በአንድ ልጁ በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፤ ከድንግል ማርያም በተወለደ፤ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መከራ በተቀበለ፤ በተሰቀለ፤ በሞተ፤ በተቀበረ፤ ወደ ሴኦል በወረደ፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን በተነሣ፤ ወደ ሰማይ በወጣ፤ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በተቀመጠ፤ በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ከዚያ በሚመለስ፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ።

ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ በአንዲት ቅድስት የሓዋርያት ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳን አንድነት፤ በኃጢአት ስርየት፤ በሥጋ ትንሣኤ፤ በዘላለም ሕይወት አምናለሁ። አሜን።

--------------------

እኛ ሁሉን በሚችል ሰማይና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን። ደግሞም በአንድ ልጁ በመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ፤ ከድንግል ማርያም በተወለደ፤ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መከራ በተቀበለ፤ በተሰቀለ፤ በሞተ፤ በተቀበረ፤ ወደ ሴኦል በወረደ፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን በተነሣ፤ ወደ ሰማይ በወጣ፤ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በተቀመጠ፤ በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ከዚያ በሚመለስ፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን።

ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ በአንዲት ቅድስት የሓዋርያት ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳን አንድነት፤ በኃጢአት ስርየት፤ በሥጋ ትንሣኤ፤

# የክርስቲያን ሃይማኖት መግለጫ

በዘላለም ሕይወት እናምናለን። አሜን።

## ፪፡ የኒቅያ የሃይማኖት መግለጫ።

ሁሉን በሚችል ሰማይንና ምድርን፣ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ።

እርሱ ብቻ የአብ ልጅ በሚሆን፣ ዓለም ሳይፈጠር ከአብ በተወለደ፣ ከአምላክ በተገኘ አምላክ፣ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፣ ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ፣ በህልውናው ከአብ ጋር አንድ የሆነ፣ በተፈጠረ ሳይሆን በተወለደ፣ ሁሉ በእርሱ በሆነ፣ ስለ እኛ ስለ ሰዎች ስለ ደህንነታችንም ከሰማይ በወረደ፣ በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም ስጋ ነስቶ ሰው በሆነ፣ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ በተሰቀለ፣ መከራ በተቀበለ፣ በሞተ፣ በተቀበረም፣ በቅዱሳት መጻሕፍትም እንደተጻፈ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሣ፣ ወደ ሰማይም በወጣ፣ በአብ ቀኝ በተቀመጠ፣ በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ዳግመኛ በክብር በሚመጣ፣ ለመንግሥቱም ፍጻሜ በሌለው በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ።

ከአብና ከወልድ ጋር በሚሰገድለትና በሚከበር፣ ከአብና ከወልድ በሚሠርጽ፣ በነቢያት በተነገረ፣ የሕይወት ጌታና ሰጪ በሆነ፣ በመንፈስ ቅዱስም አምናለሁ።

የሁሉም በሆነች በአንዲት ቅድስት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንም አምናለሁ። ለኃጢአት ማስተስረያ በአንዲት ጥምቀትም አምናለሁ። የሙታንን ትንሣኤና ገና የሚመጣውን ዓለም ሕይወትም እጠባበቃለሁ። አሜን።

# የክርስቲያን ሃይማኖት መግለጫ

## ፫፡ የአትናቴዎስ የሃይማኖት መግለጫ።

1. ለመዳን የሚፈልግ ሁሉ ከሁሉም ነገር አስቀድሞ የሁሉ የሆነች የቤተ ክርስቲያንን ሃይማኖት እውነተኛ አድርጎ ሊቀበል ያስፈልገዋል።

2. ንጹሕና ሙሉ አድርጎ ያልጠበቀው ሁሉ ያለ ጥርጥር የዘላለም ጥፋት ይደርስበታል።

3. በሦስትነቱ አንድነቱን፥ በአንድነቱም ሦስትነቱን አምነን አንድ አምላክን እናመልካለን። ይህም እውነተኛ የክርስትና ሃይማኖት ነው።

4. ይህንንም የምናደርገው አካላቱን ሳንደባልቅ መለኮታዊ ህልውናውንም ሳንከፍል ነው።

5. ምክንያቱም የአብ አካል ለብቻው የወልድ ለብቻው፥ የመንፈስ ቅዱስም ለብቻው ስለሆነ ነው።

6. ሆኖም፥ የአብ፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ መለኮት አንድ ነው፥ ክብሩ ሥልጣኑም እኩል ሆኖ ይኖራል።

7. ወልድ በህልውናው እንደ አብ ነው፥ መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ ነው።

8. አብ አልተፈጠረም፥ ወልድ አልተፈጠረም፥ መንፈስ ቅዱስም አልተፈጠረም።

9. አብ ወሰን የለውም፥ ወልድ ወሰን የለውም፥ መንፈስ ቅዱም ወሰን የለውም።

10. አብ ዘላለማዊ የሚሆን አንድ እንጂ ሦስት አይደሉም።

11. ቢሆንም ዘላለማዊ የሚሆን አንድ እንጂ ሦስት አየደሉም።

12. ያልተፈጠና ወሰን የሌለው ሦስት እንዳልሆነ እንደዚሁም ያልተፈጠረና ወሰን የሌለው አንድ ነው።

13. እንዲሁም አብ ሁሉን የሚችል ነው፥ ወልድ ሁሉን የሚችል ነው፥ መንፈስ ቅዱስም ሁሉን የሚችል ነው።

14. ቢሆንም፥ ሁሉን የሚችል አንድ አንጂ ሦስት አይደለም።

15. ስለዚህ አብ አምላክ ነው፥ ወልድ አምላክ ነው፥ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው።

16. ሆኖም አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይደሉም

17. ስለዚህ አብ ጌታ ነው፥ ወልድ ጌታ ነው፥ መንፈስ ቅዱስም ጌታ ነው።

18. ሆኖም አንድ ጌታ እንጂ ሦስት ጌቶች አይደሉም።

19. ምክንያቱም የክርስትና እምነት እውነተኛነት እያንዳንዱ አካል አምላክና ጌታ መሆኑን እንድናምን እንደሚያስገድደን ሁሉ የክርስትና ሃይማኖት ሦስት አማልክት ወይም ሦስት ጌቶች እንዳንል ይከለክለናል።

20. አብ በማንም አልተሠራም፥ አልተፈጠረም፥ አልተወለደምም።

21. ወልድ ከአብ ተወለደ እንጂ አልተሠራም አልተፈጠረምም።

22. መንፈስ ቅዱ አልተሠራም፥ አልተፈጠረም፥ አልተወለደምም፥ ነገር ግን ከአብና ከወልድ የሚሠርጽ ነው።

23. ስለዚህ አብ አንድ ስለሆነ ሦስት አብ አይደለም፥ ወልድም አንድ

እንጂ ሦስት ወልድ አይደለም፥ መንፈስ ቅዱስም አንድ እንጂ ሦስት አይደለም።

24. ከሦስቱ አካላት አንዱ ከሌለው ቀዳሚነት ወይም ደኃሪነት የለውም፥ አንዱም ከሌላው የሚበልጥ ወይም የሚያንስ አይደለም።

25. ስለሆነም፥ ሦስቱ አካላት በእኩልነትና በዘላለማዊነት አንድ ናቸው። ከዚህ የተነሣም ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ሦስቱ አካላት በአንድ መለኮት አንድ አምላክም በሦስት አካላት ይመለካል።

26. ለመዳን የሚፈልግ ሁሉ ስለ ሥላሤ እንደዚህ ማሰብ ይገባዋል።

27. ስለዚህ ሌላ የዘላለምን ደኅንነት ለማግኘት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ መገለጽ በእውነት ማመን አስፈላጊ ነው።

28. ምክንያቱም ትክክለኛው እምነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ አምላክም ሰውም መሆኑን ማመን አስፈላጊ ነው።

29. እርሱም ከዘመናት አስቀድሞ ከአብ የተወለደ አምላክ ከእናቱም በሥጋ በዓለም የተወለደ ሰው ነው።

30. የሚያስብ ነፍስ ያለችውና የሰውን ሥጋ የለበሰ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው።

31. በአምላክነቱ ከአብ ጋር የተካከለ፥ በሰውነቱም ከአብ ያነሰ ነው፤

32. አምላክም ሰውም ቢሆንም አንድ ክርስቶስ እንጂ ሁለት ክርስቶስ አይደለም።

33. አንድ ነው ስንል ግን የሰውን ሥጋ ለበሰ እንጂ መለኮት ወደ ሥጋ አልለወጠም።

34. በእርግጥ አንድ የሆነውም በባሕርያት መደባለቅ ሳይሆን በአካል አንድ በመሆኑ ነው።

35. ምክንያቱም የሚያስብ ነፍስና ሥጋ አንድ ሰው እንደሆኑ ሁሉ አምላክና ሰው በክርስቶስ አንድ ናቸው።

36. እርሱም ለደህንነታችን ሲል መከራ ተቀበለ፥ ወደ ሲኦል ወረደ፥ ከሙታን ተነሣ።

37. ወደ ሰማይ የወጣ፥ በአብ ቀኝ የተቀመጠ፥ በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ከዚያ የሚመለስ፥

38. በመምጣቱ ጊዜም ሰዎች ሁሉ በሥጋ ተነስተው ስለ ሥራቸው መልስ ይሰጣሉ።

39. መልካም የሠሩ ወደ ዘላለም ሕይወት ክፉ የሠሩም ወደ ዘላለም እሳት ይገባሉ።

40. ይህ እውነተኛው የክርስትና እምነት ነው። ይህን የሚያምንና አጥብቆ የማይዝ ሊድን አይችልም።

## ➤የአትናቴዎስ የሃይማኖት መግለጫ

### ✔ሁሉንም ሰው የሚያስማማ

1- ለመዳን የሚፈልግ ሁሉ ከሁሉም ነገር አስቀድሞ የሁሉ የሆነች የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትን እውነተኛ አድርጎ ሊቀበል ያስፈልገዋል።

# የክርስቲያን ሃይማኖት መግለጫ

2- ንጹሕና ሙሉ አድርጎ ያልጠበቀው ሁሉ ያለ ጥርጥር የዘላለም ጥፋት ይደርስበታል።

3- በሦስትነቱ አንድነቱን፥ በአንድነቱም ሦስትነቱን አምነን አንድ አምላክን እናመልካለን። ይህም እውነተኛ የክርስትና ሃይማኖት ነው።

4- ይህንንም የምናደርገው አካላቱን ሳንደባልቅ መለኮታዊ ህልውናውንም ሳንከፍል ነው።

5- ምክንያቱም የአብ አካል ለብቻው የወልድ ለብቻው፥ የመንፈስ ቅዱስም ለብቻው ስለሆነ ነው።

6- ሆኖም የአብ፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱ መለኮት አንድ ነው፥ ክብሩ ሥልጣኑም እኩል ሆኖ ይኖራል።

7- ወልድ በህልውናው እንደ አብ ነው፥ መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ ነው።

8- አብ አልተፈጠረም፥ ወልድ አልተፈጠረም፥ መንፈስ ቅዱስም አልተፈጠረም።

9- አብ ወሰን የለውም፥ ወልድ ወሰን የለውም፥ መንፈስ ቅዱም ወሰን የለውም።

10- አብ ዘላለማዊ ነው፥ ወልድ ዘላለማዊ ነው፥ መንፈስ ቅዱስም ዘላለማዊ ነው።

11- ቢሆነም ዘላለማዊ የሚሆን አንድ እንጂ ሦስት አይደሉም።

12- ያልተፈጠረና ወሰን የሌለው ሦስት እንዳልሆነ እንደዚሁም ያልተፈጠረና ወሰን የሌለው አንድ ነው።

13- እንዲሁም አብ ሁሉን የሚችል ነው፥ ወልድ ሁሉን የሚችል ነው፥ መንፈስ ቅዱስም ሁሉን የሚችል ነው።

14- ቢሆንም፥ ሁሉን የሚችል አንድ እንጂ ሦስት አይደሉም።

15- ስለዚህ አብ አምላክ ነው፥ ወልድ አምላክ ነው፥ መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው።

16- ሆኖም አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይደሉም።

17- ስለዚህ አብ ጌታ ነው፥ ወልድ ጌታ ነው፥ መንፈስ ቅዱስም ጌታ ነው።

18- ሆኖም አንድ ጌታ እንጂ ሦስት ጌቶች አይደሉም።

19- ምክንያቱም የክርስትና እምነት እውነተኛነት እያንዳንዱ አካል አምላክና ጌታ መሆኑን እንድናምን እንደሚያስገድደን ሁሉ የክርስትና ሃይማኖት ሦስት አማልክት ወይም ሦስት ጌቶች እንዳንል ይከለክለናል።

20- አብ በማንም አልተሠራም፥ አልተፈጠረም፥ አልተወለደምም።

21- ወልድ ከአብ ተወለደ እንጂ አልተሠራም አልተፈጠረምም።

22- መንፈስ ቅዱስ አልተሠራም፥ አልተፈጠረም፥ አልተወለደምም፥ ነገር ግን ከአብ የሚሠርጽ ነው።

23- ስለዚህ አብ አንድ ስለሆነ ሦስት አብ አይደለም፥ ወልድም አንድ እንጂ ሦስት ወልድ አይደለም፥ መንፈስ ቅዱስም አንድ እንጂ ሦስት አይደለም።

24- ከሦቱ አካላት አንዱ ከሌላው ቀዳሚነት ወይም ደኃሪነት የለውም፤ አንዱም ከሌላው የሚበልጥ ወይም የሚያንስ አይደለም።

25- ስለሆነም፥ ሦስቱ አካላት በእኩልነትና በዘላለማዊነት አንድ ናቸው። ከዚህ የተነሣም ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ሦስቱ አካላት በአንድ መለኮት አንድ አምላክም በሦስት አካላት ይመለካል።

26- ለመዳን የሚፈልግ ሁሉ ስለ ሥላሴ እንደዚህ ማሰብ ይገባዋል።

27- ከዚህም ሌላ የዘላለምን ደኅንነት ለማግኘት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ መገለጽ በእውነት ማመን አስፈላጊ ነው።

28- ምክንያቱም ትክክለኛው እምነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ አምላክም ሰውም መሆኑን አምነን ማስታወቅ ነው።

29- እርሱም ከዘመናት አስቀድሞ ከአብ የተወለደ አምላክ ከእናቱም በሥጋ በዓለም የተወለደ ሰው ነው።

30- የሚያስብ ነፍስ ያለችውና የሰውን ሥጋ የለበሰ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው።

31- በአምላክነቱ ከአብ ጋር የተካከለ፥ በሰውነቱም ከአብ ያነሰ ነው።

32- አምላክም ሰውም ቢሆንም አንድ ክርስቶስ እንጂ ሁለት ክርስቶስ አይደለም።

33- አንድ ነው ስንል ግን የሰውን ሥጋ ለበሰ እንጂ መለኮት ወደ ሥጋ አልተለወጠም።

34- በእርግጥ አንድ የሆነውም በባሕርያት መደባለቅ ሳይን በአካል አንድ በመሆኑ ነው።

35- ምክንያቱም የሚያስብ ነፍስና ሥጋ አንድ ሰው እንደሆኑ ሁሉ አምላክና ሰው በክርስቶስ አንድ ናቸው።

36- እርሱም ለደህንነታችን ሲል መከራ የተቀበለ፥ ወደ ሲኦል የወረደ፥ ከሙታን የተነሣ፤

37- ወደ ሰማይ የወጣ፥ በአብ ቀኝ የተቀመጠ፥ በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ከዚያ የሚመለስ ነው።

38- በመምጣቱ ጊዜም ሰዎች ሁሉ በሥጋ ተነስተው ስለ ሥራቸው መልስ ይሰጣሉ።

39- መልካም የሠሩ ወደ ዘላለም ሕይወት ክፉ የሠሩም ወደ ዘላለም እሳት ይገባሉ።

40- ይህ እውነትኛው የክርስትና እምነት ነው። ይህን የማያምንና አጥብቆ የማይዝ ሊድን አይችልም።